የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ — ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 34
ADDIS ABABA - 22nd April, 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፸፩/፲፱፻፹፱ ዓ·ም·
ለ፯ኛው የቴሌኮሙኒኬሽን የልማት መርሐ ግብር ክፊል ማስፈጸሚያ ከኖርድባንከን ለተገኘው ብድር ዋስትና የተሰጠበት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................... ገጽ ፭፻፲፪

## CONTENTS

Proclamation No. 71/1997
Nordbanken Loan, for Partly Financing the 7th Telecommunications Development Programme, Guaranteeing Agreement Ratification proclamation ........................................................ Page 512

### አዋጅ ቁጥር ፸፩/፲፱፻፹፱

### ከኖርድባንከን ለተገኘው ብድር ዋስትና የተሰጠበትን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለ፯ኛው የቴሌኮሙኒኬሽን የልማት መርሐ ግብር ክፊል ማስፈጸሚያ የሚውል የ፩፻፲፪ ሚሊዮን ፭፻ሺህ (የአንድ መቶ አሥራ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) ክሮነር የብድር ስምምነት በስዊድን ኖርድባንከን እና በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን መካከል የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም በአዲስ አበባ ላይ የተፈረመ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገንዘብ ሚኒስቴርም በዋስትና ሰጭነት የተጠቀሰውን ስምምነት ስለተፈረመ ፤

ይህንኑ ዋስትና የተሰጠበትን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለ፯ኛው የቴሌኮሙኒኬሽን የልማት መርሐ ግብር ክፊል ማስፈጸሚያ ከኖርድባንከን ለተገኘው ብድር ዋስትና የተሰጠበት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፸፩/፲፱፻፹፱ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 71/1997

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT OF GUARANTEE TO THE NORDBANKEN LOAN

*WHEREAS,* a Loan Agreement in the amount of 112,500,000 SEK (one hundred twelve million five hundred thousand Swedish Kroner), for partly financing the 7th Telecommunications Development Programme, was signed between the Ethiopian Telecommunications Corporation and the Swedish Nordbanken, in Addis Ababa, on the 15th day of February, 1997;

*WHEREAS,* the Ministry of Finance had also signed said Agreement as a guarantor, on behalf of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

*WHEREAS,* the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said guaranteeing agreement at its session held on the 22nd day of April, 1997;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Nordbanken Loan, for Partly Financing the 7th Telecommunications Development Programme, Guaranteeing Agreement Ratification Proclamation No. 71/1997."

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "ስምምነት" ማለት የስዊድን ኖርድባንከን በአበዳሪነት ፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን በተበዳሪነት እንዲሁም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገንዘብ ሚኒስቴር በዋስትና ሰጪነት የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የተፈራረሙት ስምምነት ነው ።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትር በስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በዋስትናው የተጠየቀ እንደሆነ ክፍያ እንዲያደርግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Agreement" means the Agreement signed in Addis Ababa by and between the Nordbanken as lender, the Ethiopian Telecommunications Corporation as borrower and the Ministry of Finance of the Federal Democratic Republic of Ethiopia as guarantor, on the 15th day of February, 1997.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby authorized to make payments as per the terms and conditions of said Agreement should it become necessary under the guarantee provided therein.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 22nd day of April, 1997.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of April, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE